# ዓለም አቀፍ የፀረ-ጉቦኝነት ሕግ ማስከበሪያ ፖሊሲ

## *የፖሊሲው አጠቃላይ መግለጫ*

ይህ ፖሊሲ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ግልጽ የሆነ ማዕቀፍ በማስቀመጥ PepsiCo በሁሉም የንግድ ስራ ግንኙነቶቹ ላይ ስነ-ምግባር ባለውና ሃላፊነት በተሞላበት መንገድ የመንቀሳቀስ ግዴታ እንዳለበት አጽንኦት ይሰጣል፡

- የመንግስት ዘርፍና የንግድ ነክ ጉቦኝነትን የሚከለክል
- በሶስተኛ ወገኖች ላይ የሚተገበሩ አሰፈላጊ የፀረ-ሙስና ሒደቶችን የሚያስተናግድ
- ከመንግስት የስራ ሃላፊዎች ጋር በተያያዘ ስጦታዎች፣ ምግብ፣ ጉዞ እና መዝናኛዎችን አስመልክቶ መከበር ያለባቸውን ደንቦች የሚያብራራ
- ከመንግስት ተወካይ ጋር ለሚደረጉ ልገሳዎች፣ ስፖንሰርሺፖችና የኮርፖሬት ማሕበራዊ ሃላፊነት (CSR) ተግባራትን ተፈላጊ ሁኔታዎች የሚዘረዝር
- ለሁሉም የ PepsiCo ግብይቶች ትክክለኛ መዛግብትና ሂሳቦች መያዛቸው ላለው ጠቀሜታ አጽንኦት ይሰጣል

የ PepsiCo **ዓለም አቀፍ የፀረ-ጉቦኝነት ሕግ ማስከበሪያ ፖሊሲ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች** እነዚህን አበይት አርእስት በተመለከተ ስለእያንዳንዳቸው የበለጠ ዝርዝር መመሪያ የያዙ ናቸው። በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች እዚህ እና በሕግ ማስከበር እና ስነ-ምግባር መነሻ ገጽ myPepsiCo.com (የ C&E መነሻ ገጽ) ላይ ይገኛሉ።

## *የፖሊሲው ተፈጻሚነት*

ይህ ፖሊሲ በሁሉም የ PepsiCo ተባባሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ ሲባል፣ የ PepsiCo ተባባሪዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- በመላው ዓለም ላይ የሚገኙ ሁሉም የ PepsiCo ተባባሪዎች (የንኡስ ድርጅቶቻችን ሰራተኞችን ጨምሮ)
- የ PepsiCo የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በቦርድ አባልነታቸው ሃላፊነት በሚንቀሳቀሱበት ወቅት
- የማንኛዉም ጆይንት ቬንቸር ሰራተኞች፣ ሃላፊዎች እና ዳይሬክተሮች ወይም አብዛኛውን ባለቤትነት ወይም የስራ አመራር ቁጥጥር በ PepsiCo ስር የሆነ ማንኛውም ተባባሪ ድርጅት (ለምሳሌ፡- የተጠናከሩ ቅርንጫፎች )

በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ያሉ ድንጋጌዎች *እንዳግባብነቱ በ PepsiCo የአቅራቢዎች የአሰራር ደንብ በሚገዙ* በሁሉም ሶስተኛ ወገኖች ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

### **የመንግስት የስራ ሃላፊ የሚባለው ማነው?**

- ሁሉም የመንግስት ተቀጣሪዎች፡ የተቆጣጣሪ ድርጅቶች፣ መምሪያዎች፣ የሚኒስቴር መ/ቤቶችና ሌሎች እንደ ዩኒቨርሲቲ ያሉ የመንግስት አካላት ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ማለትም እንደ ጉምሩክ ሃላፊዎችና ጸሐፊዎች፣ እንደዚሁም ተቆጣጣሪዎችን የመሳሰሉ ሲቪል ሰራተኞች
- ለመንግስት የሃላፊነት ቦታ የሚወዳደር እጩ (ከዚህ በፊት ተመራጭ ባይሆንም እንኳን)
- የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይ የፖለቲካ ፓርቲ ሃላፊ
- ከንቲባዎች፣ ኮሚሽነሮችና የማዘጋጃ ቤት የቦርድ አባላትን ጨምሮ በየትኛውም የመንግስት ደረጃ ላይ ያሉ ተመራጭ ባለስልጣናት
- የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች፡- ለምሳሌ የዓለም ጤና ድርጅትና የዓለም ባንክ
- የሕግ አስከባሪ/ፖሊስ እና የጦር ሰራዊት አባላት
- የመንግስት ንብረት የሆኑ የባቡር አገልግሎቶች፣ አየር መንገዶች፣ ሆስፒታሎችና ላብራቶሪዎች፣ የነዳጅ ማደያዎች ወይም ማረሚያ ቤቶችን የመሳሰሉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች
- የንጉሳውያን ቤተሰቦች አባላት
- የዓለም አቀፍ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሰራተኞች
- ከላይ የተዘረዘሩት አካላት የትዳር ጓደኞች ወይም የቅርብ የቤተሰብ አባላት

### **ጉቦ ምንድን ነው?**

ጉቦ ማለት ማንኛውም የተፈጸመ ወይም ለመፈጸም የታሰበ ዋጋ ያለው ማንኛውም ነገር ለመንግስት የስራ ሃላፊ ወይም በግል ወይም በንግድ ዘርፍ ውስጥ ላለ ማንኛውም ሰው ወይም አካል የሚሰጥ ማንኛዉም ክፍያ ወይም ለመክፈል የቀረበ ክፍያ ሲሆን ዓላማውም ተቀባዩ ሃላፊነቱን ያለአግባብ እንዲጠቀም ወይም ኢ-ፍትሐዊ የንግድ ስራ ጥቅም ለማግኘት ወይም ጠብቆ ለማቆየት የታሰበ ነው

### **ዋጋ ያለው ማንኛውም ነገር ምን ማለት ነው?**

ዋጋ ያለው ማንኛውም ነገር ማለት ጥሬ ገንዘብ፣ በምርት ወይም በጥሬ ገንዘብ መቀየር የሚችሉ የጥሬ ገንዘብ ባህርይ ያላቸው የስጦታ ካርዶች፣ ቫውቸሮች፣ ስጦታዎች፣ መስተንግዶዎች፣ ምግቦች፣ ዕቃዎች፣ አገልግሎቶች ወይም ሽቀጣ ሸቀጥ፣ የዝግጅት መግቢያ ትኬቶች፣ የችርቻሮ የምስክር ወረቀቶች፣ መዝናኛ፣ የጉዞ ትኬት፣ የሽርሽር ቤቶችን መጠቀም፣ የአየር ትኬት ወይም የመስተንግዶ አገልግሎቶች፣ ለጓደኞችና ለዘመዶች የሚመቻቹ ትምህርታዊ፣ የስራ ወይም የስራ ላይ ልምምድ ዕድሎችን የመሳሰሉ ውለታዎች፣ የአክሲዮን አማራጮች፣ ለተመረጡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚሰጡ ልገሳዎች፣ የዋጋ ቅናሾች፣ የግል አገልግሎቶች፣ ብድሮች፣ የብድር ግዴታን አብሮ መፈረም ወይም ለወደፊት የስራ ዕድል ለመስጠት ቃል መግባት ነዉ

## 1.0 ጉቦ እና የማቀላጠፊያ ክፍያዎች

ማንኛውም የ PepsiCo ተባባሪ ጉቦ ወይም ማቀላጠፊያ ክፍያ መስጠት ወይም የመስጠት ጥያቄ ማቅረብ የለበትም። PepsiCo የማቀላጠፊያ ክፍያዎችን የማይፈቅድ ሲሆን፣ እንዲህ ዓይነት ክፍያዎችም በሕግ ቢፈቀዱም እንኳን ይህን ፖሊሲ የሚጥሱ ናቸው። በዚሁ መሰረት፣ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ጉቦን በተመለከተ የተጠቀሱ ነገሮች ሁሉ የማቀላጠፊያ ክፍያንም ይጨምራሉ።

> ***ማቀላጠፊያ ክፍያ ምንድን ነው?***
>
> ማቀላጠፊያ ክፍያ ማለት ለመንግስት የስራ ሃላፊ የሚከፈል ሆኖ ይህም የፖሊስ ጥበቃ ወይም የመልእክት አገልግሎት ማቅረብ፣ ቪዛ፣ ፈቃድ ወይም የፈቃድ ማመልከቻዎችን ማመቻቸት፣ ዕቃዎችን በጉምሩክ በኩል ማስተላለፍ፣ ወይም የስልክ፣ የውሃና የመብራት አገልግሎቶችን ማቅረብ የመሳሰሉትን በአንድ ግለሰብ ውሳኔ የማይፈጸሙ አገልግሎቶችን ለማቀላጠፍ የሚከፈል ነው፤ እንዲህ ዓይነት ክፍያ በ PepsiCo አይፈቀድም

የ PepsiCo ተባባሪዎች ጉቦ አለመክፈል በጤናቸው ወይም ደህንነታቸው ላይ የቅርብ ስጋት የሚጋርጥ ካልሆነ በስተቀር ጉቦ በጭራሽ መክፈል የለባቸውም። አደገኛ ሁኔታን ለማስቀረት ሲባል የሚከፈሉ ሁሉም የጉቦ ክፍያዎችና የጉቦ ጥያቄዎች (ክፍያው በተጨባጭ የተፈጸመ ሆነም አልሆነም) ለአካባቢው የሕግ ማስከበርና የስነ ምግባር መኮንን ወይም ለአካባቢዎ የሕግ መምሪያ ወዲያውኑ ሪፖርት መደረግ አለባቸው። ከታች በክፍል 5.0 ውስጥ እንደተብራራው፣ ሁሉም ክፍያዎች በትክክል መመዝገብ አለባቸው።

## 2.0 ከሶስተኛ ወገኖች ጋር የተያያዙ የጉቦኝነት ስጋቶች

> ***ሶስተኛ ወገን ምንድን ነው?***
>
> በዚህ ፖሊሲ መሰረት፣ ሶስተኛ ወገን ማለት PepsiCo የሚቀጥረው ማንኛውም ግለሰብ ሲሆን እነርሱም አቅራቢዎች፣ ወኪሎች፣ አማካሪዎች፣ አገልግሎት ሰጪዎች ወይም አገልግሎት አቅራቢዎችን የመሳሰሉት ናቸው። ምርቶችን ከ PepsiCo በድርድር ዋጋ ገዝተው ባለቤትነቱን የሚረከቡና ድርድር በተደረገባቸው የ PepsiCo ደንቦችና ሁኔታዎች መሰረት ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች የሚሸጡ አከፋፋዮችም እንደ ሶስተኛ ወገኖች ይቆጠራሉ

በ PepsiCo ስም ለመንግስት የስራ ሃላፊ ጉቦ ለመስጠት ሃሳብ ለሚያቀርቡ ወይም ጉቦ ለሚከፍሉ ሶስተኛ ወገኖች ተግባር PepsiCo ተጠያቂ ሊደረግ ይችላል። በ PepsiCo ሶስተኛ ወገኖች በኩል የሚፈጸም የጉቦ ክፍያ ክልክል ነው። የሶስተኛ ወገን ተግባራት ጉቦ መክፈልን ወይም ለመክፈል ሃሳብ ማቅረብን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ የሚያሳዩ የማስጠንቀቂያ ምልክቶችንም ችላ ማለት ይህን ፖሊሲ መጣስ ነው።

### የሶስተኛ ወገን የስጋት ስራ አመራር (TPDD)

PepsiCo ስጋት ተኮር የጸረ-ሙስና የተገቢ ትጋት ፕሮግራም(due diligence program) ያለው ሲሆን፣ ይህም የሶስተኛ ወገን የስጋት ስራ አመራር (TPDD) በመባል ይታወቃል። ስለ TPDD ተጨማሪ ዝርዝር፣ ባለ አምስት ደረጃ የ TPDD ሒደትን ጨምሮ በ **PepsiCo የ TPDD ሒደት አጠቃላይ መግለጫ፣ እዚህና በ C&E መነሻ ገጽ ላይ** ሊገኝ ይችላል ወይም ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ ዓለም አቀፍ የሕግ ማስከበርና ስነ-ምግባርን ያነጋግሩ።

ማስታወሻ: አስፈላጊ የሆኑ ሁሉም የፀረ-ሙስና ማጣራት ሒደቶች እስከሚጠናቀቁ ድረስ ማንኛውም የ PepsiCo ተባባሪ ከሶስተኛ ወገን ጋር ግንኙነት ማድረግ የለበትም። የ PepsiCo ተባባሪዎች የአገልግሎት አቅራቢን መረጃ በሚያደራጁበት ወቅት አግባብነት ያለው TPDD ስለመጠናቀቁ ደጋፊ የሰነድ ማስረጃዎችን ማቅረብ አለባቸው.

## 3.0 ለመንግስት ባለስልጣናት የሚሰጡ ስጦታዎች፣ ምግቦች፣ ጉዞ እና መዝናኛ*

**ለደንበኞች ወይም ከደንበኞች፣ አቅራቢዎች እና ሌሎች ሶስተኛ ወገኖች የሚሰጡ የቢዝነስ ስጦታዎችን በተመለከተ ዝርዝር መስፈርቶችን ለማየት፣ እባክዎ ዓለም አቀፍ የቢዝነስ ስጦታዎችን ፖሊሲ ይመልከቱ።*

ስጦታዎች፣ ምግቦች፣ ጉዞ እና መዝናኛ በመንግስት የስራ ሃላፊዎች ላይ ያልተገባ ተጽእኖ የማሳደር አቅም አላቸው። ስለዚህ፣ የ PepsiCo ተባባሪዎች በአጠቃላይ ለመንግስት የስራ ሃላፊ ስጦታዎች ወይም የመስተንግዶ ግብዣ ከማድረግ መቆጠብ አለባቸው። ይሁን እንጂ፣ በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ምክንያታዊ የሆነ ስጦታ ወይም መስተንግዶ ለመንግስት የስራ ሃላፊ እንዲሰጥ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች አሉ፤ እነርሱም፡

(1) የወጣው ወጪ ከታች የተቀመጡትን ተከታታይ ዝቅተኛ መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ፤ እና

(2) የ PepsiCo ተባባሪ **ከአካባቢው የሕግ ማስከበርና የስነ ምግባር መኮንን ወይም ከአካባቢው የሕግ መምሪያ በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ከተሰጠው**

## የመንግስት የስራ ሃላፊዎችን የሚመለከቱ ዝቅተኛ የወጪ መስፈርቶች[1]

ለመንግስት የስራ ሃላፊ ስጦታ ወይም መስተንግዶ ከማቅረብዎ በፊት ቢያንስ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላቱን ያረጋግጡ፡

- በቅን ልቦና መሰጠቱንና በምላሹ ምንም ዓይነት ውለታ ወይም ያልተገባ ጥቅማ ጥቅም የንግድ ስራ ጥቅም ለማግኘት የማይጠብቅ መሆኑን
- ምክንያታዊ**እና የተለመደ መሆኑን፤ ማለትም ለሙያዊ ክብር ባጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸው ደረጃዎችን የሚያሟላ መሆኑን
- በሚታይና ግልጽ በሆነ መንገድ መሰጠቱን
- ያልተገባ መልክ እንዳይኖረው ለማስቻል ሲባል ተደጋጋሚ ባልሆነ መልኩ መሰጠቱን
- በሃገሪቱ ሕጎችና ደንቦች መሰረት የሚፈቀድ መሆኑን

*ለመስተንግዶ ምክንያታዊ ወጪን በሚወስኑበት ወቅት፣ የ**PepsiCo ዓለም አቀፍ የጉዞ እና መዝናኛ ፖሊሲ ክፍል 4.5.1 እና አባሪዎች ውስጥ የተቀመጡትን ዓለም አቀፋዊ የክፍያ ጣሪያዎችን ከግምት ውስጥ ያስገቡ።**

| ለመንግስት የስራ ሃላፊዎች የሚሰጥ ማንኛውም ስጦታ የሚከተሉትን ተጨማሪ መስፈርቶችም ማሟላት አለበት፡ | ለመንግስት የስራ ሃላፊዎች የሚሰጥ ማንኛውም መስተንግዶ የሚከተሉትን ተጨማሪ መስፈርቶችም ማሟላት አለበት፤ |
|---|---|
| • ዋጋው ትንሽ መሆን አለበት (በአጠቃላይ ከ $75.00 ዩ ኤስ ዶላር በታች) | • የንግድ ስራ ዓላማው ተአማኒ/ተቀባይነት ያለዉ መሆን አለበት |
| • መሰጠት ያለበት በማንኛውም ግለሰብ ስም ሳይሆን በ PepsiCo መሆን አለበት | • ከ PepsiCo የንግድ ስራ ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ወይም ግንኙነት ሊኖረው ይገባል |

## በጽሑፍ የሚሰጥ የቅድሚያ ፈቃድ

ሁሉም የመንግስት ሃላፊዎች የስጦታ፣ የምግብ፣ የጉዞ እና የመዝናኛ የቅድመ ፈቃድ ጥያቄዎች መቅረብ ያለባቸው እዚህ ወይም በ C&E መነሻ ገጽ ላይ ያለውን አጭር ኦንላይን ቅጽ (የቅድሚያ ፈቃድ ቅጽ) በመሙላት ነው።

## ከቅድሚያ ፈቃድ ግዴታ ነጻ የሆኑ ጉዳዮች

*ተፈጻሚነት ያላቸው የሃገር ውስጥ ሕጎችና ደንቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣* ከመንግስት ሃላፊዎች ጋር ለተያያዙ ወጪዎች የቅድሚያ ፈቃድ የማያስፈልገው በሚከተሉት ውስን ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ ነው፡

[1] ከዘመቻ ፋይናንስ፣ የመንግስት ስነ-ምግባር፣ የውትወታና ይፋ ማድረጊያ ሕጎች ጋር የተያያዙ የተናጠል ፈቃዶች አስፈላጊ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ምክንያቱም ሃገር ተኮር ሕጎችና ደንቦች በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ከተዘረዘሩት የሚለዩ ገደቦችና የማይካተቱ ነገሮችን ሊያስቀምጡ ይችላሉ።

- ዋጋቸው ለአንድ የመንግስት ሃላፊ
  $75.00 ዩኤስ ዶላር ወይም ያነሰ የሆኑ (ለአንድ የመንግስት ሃላፊ በዓመት ከ $200.00 ዩኤስዶላር፣ ለመንግስታዊ ድርጅት ደግሞ በዓመት ከ $1000.00 ዩኤስ ዶላር መብለጥ የለበትም) የ PepsiCo አርማ ያለባቸውን የማስታወቂያ ቁሳቁስ (ለምሳሌ:- አርማ ያለባቸው የጎልፍ ኳሶች፣ ቲ-ሸርቶች ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች) መስጠት (ወይም ከመንግስታዊ ተቋም ጋር በተያያዘ ከሆነ ደግሞ መለገስ፣ ከታች ክፍል 4.0 *ተመልከት*)

- በ PepsiCo ቅጥር ክልል ውስጥም ሆነ ውጭ አጠቃላይ ዋጋው $10.00 ዩኤስ ዶላር የሆነ እንደ ሳንድዊች፣ ፈሳሽ ምግብ፣ ቁርሳ ቁርስ፣ ወዘተ. ያለ ከ PepsiCo የንግድ ስራ ወቅታዊ እንቅስቃሴ ጋር ተያያዥነት እስካለው ድረስ የሚሰጠው የመስተንግዶ አገልግሎት አነስተኛ መስተንግዶ ለመንግስት ሃላፊዎች መስጠት፣

> ***የመንግስት ተቋም ምንድን ነው?***
>
> - *ማናቸውም መንግስታት፣ ተቆጣጣሪ ድርጅቶች፣ መምሪያዎች ወይም ሚኒስቴር መ/ቤቶች ለምሳሌ የደህንነት፣ የጤና፣ የታክስ፣ የፈቃድ ሰጪና የጉምሩክ ኤጀንሲዎች፣ የፖሊስ ወይም የእሳት አደጋ መከላከያ መምሪያዎችና ጦር ሰራዊት፤*
> - *ማናቸውም መንግስታዊ አካላት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች፤ ለምሳሌ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች፣ ላብራቶሪዎች፣ የቲቪ ጣቢያዎች ወይም ሆስፒታሎች፤*
> - *በአብዛኛው ባለቤትነት ባይያዝም፣ ማናቸውም መንግስት የሚቆጣጠራቸው የንግድ ድርጅቶች፤ ለምሳሌ በመንግስት አየር መንገድ ወይም በመንግስት በሚተዳደሩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ አነስተኛ ድርሻ መኖር፤*
> - *ዓለም አቀፍ የሕዝብ ድርጅቶች፤ ለምሳሌ የዓለም ጤና ድርጅት፣ የዓለም ባንክ፣ ዓለም አቀፍ የስራ ድርጅት ወይም ዓለመም አቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅቶች*
> - *የፖለቲካ ፓርቲዎች*

እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች በእያንዳንዱ አጋጣሚ ዋጋው $10.00 ዩኤስ ዶላር ወይም ከዚያ በታች ከሆነ ከየትኛውም የ PepsiCo ምንጭ ተደጋጋሚ የመስተንግዶ ወጪ እንዲወጣ አይፈቅዱም።

<u>የተመላሽ ገንዘብ የሰነድ ዝግጅት</u>

ለመንግስት የስራ ሃላፊ የተሰጠ ማንኛውም ዋጋ የሚያወጣ ነገር ተመላሽ እንዲደረግላቸው በሚጠይቁበት ወቅት፣ የ PepsiCo ታባባሪዎች የመንግስት ሃላፊውን ስም፣ ሃላፊነትና ከመንግስት ጋር ያለውን ግንኙነትና የወጪውን ዓላማ በወጪ ማስመለሻ ሪፖርታቸው ላይ በግልጽ ማሰፈር አለባቸው፤ ዋጋው ምንም ያህል ቢሆንም የወጪ ደረሰኝ ማቅረብ አለባቸው። በተጨማሪም፣ ወጪው እንዲወጣ በቅድሚያ የተሰጠው የጽሑፍ ፈቃድ መቅረብ አለበት። የ PepsiCo ተባባሪዎች በሃገር ውስጥ ወጪ ሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት (ለምሳሌ፡ Concur) ውስጥ አግባብነት ያለውን “የመንግስት የስራ ሃላፊ” የወጪ ምድብን መምረጥ አለባቸው።

በቅድሚያ የተሰጠ የጽሑፍ ፈቃድ ሳይኖር በመንግስት የስራ ሃላፊ ስም የወጡ ወጪዎችን ማንኛውም ቀጥተኛ ሪፖርት የወጪ ምለሳ ጥያቄ የ PepsiCo ሃላፊ መፍቀድ የለበትም። የ PepsiCo ሃላፊዎች የወጪ ምለሳን ከመፍቀዳቸው በፊት ትክክለኛ የቅድሚያ ፈቃድ መኖሩን እንዲያረጋግጡ ይጠየቃሉ።

## 4.0 <u>ልገሳዎች፣ ስፖንሰርሺፖች እንዲሁም የ CSR እንቅስቃሴዎች ለመንግስት ተቋማት ወይም ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ለተገናኙ</u>

የበጎ አድራጎት ልገሳዎች የሚያጠቃልሉት በጥሬ ገንዘብ፣ በንብረት ወይም በኮርፖሬት ሀብቶች (የግል ጊዜን ጨምሮ) መለገስን ነው። ለመንግስት የስራ ሃላፊ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚሰጡ የበጎ አድራጎት ልገሳዎች ወይም ስፖንሰርሺፖች አይፈቀዱም። ይሁን እንጂ፣ ለ/ከ መንግስት ተቋማት የሚሰጡ ወይም ከመንግስት የስራ ሃላፊ ጋር *በተያያዘ* የሚደረጉ ልገሳዎች ወይም ስፖንሰርሺፖች በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ሊፈቀዱ ይችላሉ። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ ሲባል፣ የልገሳ ወይም የስፖንሰርሺፕ ተቀባይ ከመንግስት የስራ ሃላፊ ጋር “የተያያዘ” ተደርጎ የሚቆጠረው ተቀባዩ አካል ባለቤትነቱ፣ አመራሩ ወይም ቀጥተኛ ቁጥጥር የሚደረግበት በመንግስት የስራ ሃላፊ መሆኑ ከታወቀ ነው፤ ይህም የመንግስት የስራ ሃላፊው የቦርድ አባል ከሆነ ነው።

ማናቸውም ልገሳዎች ለበጎ አድራጎት ዓላማ ብቻ መሰጠት አለባቸው፣ አንድ የተወሰነ የንግድ ስራ ውሳኔ ላይ ተጽእኖ የማሳደር ዓላማ ሊኖረው አይገባም። ሁሉም ስፖንሰርሺፖች መደረግ ያለባቸው ተቀባይነት ያላቸዉ የንግድ ስራ ጥቅሞችን ለማጎልበት ታስበው ነው።

የኮርፖሬት ማሕበራዊ ሃላፊነት (CSR) ተግባራት ብዙ ጊዜ ከአካባቢው መስተዳድሮች ጋር ግንኙነት ማድረግን የሚያካትቱ በመሆናቸው መንግስታዊ ተቋም ያለበት ወይም ከመንግስት የስራ ሃላፊ ጋር የተያያዘ የትኛውም የ CSR ኢኒሼቲቭ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ይሸፈናል።

ይሁን እንጂ፣ ይህ ፖሊሲ PepsiCo መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት የሚያደርጋቸውን የበጎ አድራጎት ልገሳዎች፣ ስፖንሰርሺፖች ወይም የ CSR ተግባራትን አይመለከትም። መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት የሚደረጉ ልገሳዎችን በተመለከተ ዝርዝር መስፈርቶችን ለማየት፣ ዓለም አቀፍ የልገሳዎች ፖሊሲን ያማክሩ

## የቅድሚያ ፈቃድ አስፈላጊነት

አንድ ልገሳ፣ ስፖንሰርሺፕ ወይም የ CSR ተግባር ለመንግስት የስራ ሃላፊ የሚቀርብ ከሆነ ወይም ከመንግስት የስራ ሃላፊ ጋር የተያያዘ ከሆነና ቀደም ሲል *የሕግ ግምገማ የማይደረግበት ከሆነ፣*, የአካባቢው የሕግ ማስከበርና የስነ-ምግባር መኮንን ወይም የአካባቢው የሕግ ክፍል የቅድሚያ የፅሑፍ ፈቃድ መገኘት አለበት።[2] ሁሉም የቅድሚያ ፈቃድ ጥያቄዎች በጽሑፍ መቅረብ ያለባቸው ሲሆን ለዚህም ከላይ በክፍል 3.0 ውስጥ በተገለጸው መሰረት ኦንላይን የቅድሚያ ፈቃድ ቅጽን በመሙላት ነው።

ለመንግስት ድርጅቶች የሚቀርቡ ወይም ከመንግስት የስራ ሃላፊዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የበጎ አድራጎት ልገሳዎች፣ ስፖንሰርሺፖችና የ CSR ተግባራትን በተመለከተ ተጨማሪ አግባብነት ያላቸውን መስፈርቶችን ለማግኘት፣ እባክዎ የአካባቢዎን የሕግ ማስከበር እና የስነ-ምግባር መኮንን ወይም የሕግ ክፍሉን ያናግሩ።

## 5.0 ትክክለኛ ሒሳቦችና መዛግብት

PepsiCo ግብይቶቹን በፍትሐዊነትና በትክክል የሚያንጸባርቁ መዝገቦችን ማዘጋጀትና መያዝ፣ እንደዚሁም እያንዳንዱን ግብይት በተመለከተ የተሟላ ግንዛቤ የሚፈጥር በቂ መረጃ መያዝ ይጠበቅበታል። ግብይቶች ተገቢ የሃላፊ ፈቃድ ሳይሰጥ መፈጸም የሌለባቸው ሲሆን፣ የሒሳብ መግለጫዎችን በትክክል ለማዘጋጀት በሚያስችል ግልጽ መንገድም መመዝገብ አለባቸው። ሁሉም የ PepsiCo ተባባሪዎች በስራ ድርሻና ሃላፊነቶቻቸው ላይ ተፈጻሚ የሆኑ የመዝገብና የሒሳብ አያያዝ ግዴታዎችን ማክበራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

## 6.0 የሚጠረጠሩ ጥሰቶችን ሪፖርት ማድረግ

ሁሉም የ PepsiCo ታባባሪዎች በዚህ ፖሊሲ ወይም በየትኛውም አግባብነት ያለው የፀረ-ሙስና ሕግ ላይ እንደተፈጸሙ የሚጠረጠሩ ጥሰቶችን ለአካባቢው የሕግ ማስከበር እና የስነ-ምግባር መኮንን ወይም የሕግ ክፍሉ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። እንደ አማራጭም፣ የተጠረጠሩ ጥሰቶች በ PepsiCo Speak Up መስመር በኩል ሪፖርት ሊደረጉ ይችላሉ። ለ Speak Up የስልክ መስመር የተደረጉ ሪፖርቶች በሕግ በሚፈቅዱ ሃገራት ውስጥ ስም አልባ ሊሆኑ ይችላሉ። የ PepsiCo ዓለም አቀፋዊ የፀረ-ብቀላ ፖሊሲ በዓለም አቀፍ የአሰራር ደንብ፣ በ PepsiCo ፖሊሲዎች ወይም በሕግ ላይ የተፈጸመ ጥሰት ነው ብሎ በማመኑ በቅን ልቡና ሪፖርት ያደረገ ማንኛውም ሰው ላይ የሚፈጸም የበቀል እርምጃን ይከለክላል።

## 7.0 ለፖሊሲ ጥሰቶች የሚጣል የዲስፕሊን ቅጣት

ይህን ፖሊሲ የሚጥስ ማንኛውም የ PepsiCo ታባባሪ በድርጅቱ በሚወሰነው መሰረት የቅጥርን ውልን እስከማቋረጥ የሚደርስ የዲስፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል።

---

[2] ወጪዎቹ ቅድሚያ ማጽደቅ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን እርግጠኛ ካልሆኑ፣ ከአካባቢዉ የ C&E መኮንን ወይም የአካባቢው የሕግ መምሪያ ምክር ይጠይቁ ወይም ለቅድሚያ ማጽደቅ በቀጥታ ያስገቡ።